## የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት 2ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠናቀቀ፤

## ክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልን የድርጅቱ ፕሬዚዳንት አድረጎ ዳግም መረጣቸው

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት(መኢአድ) 2ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለሶስት ቀናት ከተካሄደ በሁዋላ እሁድ ታህሳስ 17 ቀን 2003 ዓ/ም ክቡር ኢ/ር ሀይሉ ሻውል የድርጅቱ ፕሬዚዳንት አድርጎና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በመምረጥ ጉባኤው መጠናቀቁ ታውቋል።

አርብ ታህሳስ 15 ቀን የላዕላይ ምክር ቤት ምዕላት ጉባኤው ተሟልቶ ስብሰባ ሲካሄድ የዋለ ሲሆን ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርበውን ሪፖርት ሲያዳምጥ፣ በድርጅቱ ጥንካሬና ድክመት ላይ ግምገማና ውይይት ሲያደርግና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ሲነጋገር ውሎ  የተጠናቀቀ መሆኑ ተገልጿል።

ቅዳሜ  ታህሳስ 16 ቀን ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ ከመላው ኢትዮጵያ የዞንና የወረዳ የጉባኤው ተወካዮች፣ የሰራ አስፈጻሚና የላዕላይ ምክር ቤት አባሎች፣ የተጋበዙ እንግዶችና ጋዜጠኞች በተገኙበት ስብሰባው በክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የመኢአድ ፕሬዚዳንት መሪነት ሰብሳቢነት የተከፈተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነትና ለዲሞክራሲ ሲታገሉ ህይወታቸውን ለሰዉት ሰማዕታት የህሊና ጸሎት በማድረግ ሲሆን ከየዞኑ የመጡ ተወካዮች ሪፖርት ሲደመጥ እስከ ምሳ ሰዓት ድረስ የዋለ ሲሆን ከሰዓት በሁዋላ ደግሞ ዝግ ስብሰባ በማድረግ በተያዙ አጀንዳዎች ላይ ውይይት ሲያደርጉ፣ የድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫን በተመለከተ ሲነጋገሩ ውለዋል። በማግስቱ እሁድ ሰብሰባው ቀጥሎ ከውጭ የድጋፍ ድርጅቶች የተላኩ የድጋፍና የመልካም ምኞት መልእክቶች ሲተላለፉ፣ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሲወያዩ ከቆዩ በሁዋላ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባሎች ምርጫና የፕሬዚዳንት ምርጫ ተደርጓል።

በዚሁም መሰረት የድርጅቱ ፕሬዚዳንት ምርጫ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ቢቀርቡም በጉባኤው አባላት በሙሉ ክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል በፕሬዚዳንትነት እንዲቀጥሉ ቢጠየቁም የጤናና የእድሜ ጉዳይ በፕሬዚዳንትንት ለመቀጠል ስለማያስችላቸው ሀላፊነቱን ለመቀበል እንደሚቸግራችው ገልጸው ሌላ ሰው እንዲመረጥ ቢጠይቁም ጠቅላላ ጉባኤው ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለትግሉ ሲሉ ሃላፊነቱን እንዲቀበሉ በመማጸንና በከፍተኛ ደረጃ በመለመን ስላሰገደዷቸው ኢንጂነር ሀይሉ  ለሕዝብ ፍቅር ሲሉ የተቀበሉ መሆናቸውን ሲገልጹ ጉባኤው በለቅሶ፣ በደስታና በጭብጨባ ምስጋናና ደስታውን ገልጾ

የቀጠለው ምርጫ ደግሞ ም/ ፕሬዚዳንት መምረጥ ሲሆን ክቡር አቶ ያዕቆብ ልኬ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠዋል።

ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ደግሞ ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል፣ አቶ  ያዕቆብ ልኬ፣ ዶ/ር ታዲዎስ ቦጋለ፣ ወ/ሮ መሰሉ ረዳ፣ አቶ ማሙሸት አማረ፣ አቶ በለጠ ገብሬ፣ አቶ ገለቱ ዴዴሳ፣ ኢንጂነር ሽፈራው ዋለ፣ አቶ አዳሙ ረታ፣ ኮ/ል ታምሩ ጉልላት፣ ዶ/ር በዛብህ ደምሴ፣ አቶ እንድሪያስ ኤሮ፣ አቶ ጌታቸው ባያፈርስ፣ አቶ አማረ ጌቱ፣ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ፣ አቶ ግዛቸው ገ/ማርያም፣ አቶ ብርሃኑ ወልደሰንበት፣ አቶ አየናቸው ተረፈን መርጧል።

በማጠቃለያውም የጉባኤው ሚኒት ከተነበበ በሁዋላ ጉባኤው ተጠናቋል። ቀጥሎም አቶ ያዕቆብ ልኬ ንግግር ካደረጉ በሁዋላ ጋዜጣዊ መግለጫ የተሰጠ ሲሆን በመጨረሻም ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ተሰጥቶ ሲያበቃ ጉባኤው በሰላም ተጠናቋል።

የጉባኤው መክፈቻና መዝጊያ በመኢአድ ድጋፍ በካናዳ ፓልቶክ ክፍል በቀጥታ የተላለፈ ሲሆን ለድርጅቱ ፕሬዚዳንት፣ ለስራ አስፈጻሚ፣ ለመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች በሙሉ እንኳን ደስ አላቸሁ እንላለን።